www.fsc.gov.et

የሰ/መ/ቁ.144242

ግንቦት 30 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች- ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

አብዬ ካሳሁን

አመልካች - አቶ ገዛህኝ አየለ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች - 1ኛ. አቶ ኑረዲን ዓሊ - ቀረቡ

2ኛ. አቶ አይደር ከድር - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት የአሁን 1ኛ ተጠሪ አላግባብ ተይዞብኛል የሚሉት በከተማው ቀበሌ 04 አስተዳደር ክልል የሚገኘውን ቁጥሩ 027 የሆነ የቀበሌ የንግድ ሱቅ እንዲመለስላቸው ያቀረቡትን ክስ ተመልክቶ የአሁን አመልካች ሱቁን ለከሳሽ (1ኛ ተጠሪ) እንዲያስረክቡ ያሳለፈውን ውሳኔ እና ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔው ግድፈት አልተገኘበትም በማለት የቀረበለትን አቤቱታ ባለመቀበል ትዕዛዝ በመስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 29/2009 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ አከራካሪው ጉዳይ የቀበሌ ቤት ሆኖ ዕያለ የስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነው በማለት ክርክሩን አይቶ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

በበኩላችን አመልካች በዳኝነት ስልጣን ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ክሱ የቀረበው የድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 04 አስተዳደር በሚያስተዳድረው በቀበሌው ክልል የሚገኘውን ቁጥሩ 027 የሆነ የንግድ ሱቅ

ለማስመለስ ሲሆን ከክሱ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው ዳኝነት የተጠየቀው የሥር 1ኛ ተከሳሽ (የአሁን 2ኛ ተጠሪ) በከሳሽ ከተሰጠው የውክልና ስልጣን ውጪ በቤቱ በራሱ ሥም የንግድ ፍቃድ ከማውጣቱም በላይ ለ2ኛ ተከሳሽ (አሁን አመልካች) በአደራ ሰጥቶት የሚገኝ በመሆኑ እንዲመልስልኝ ብጠይቀውም ለመመለስ ፈቃደኛ ስላልሆነ ከመንግስት የተከራየሁትን የንግድ ሱቅ እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክሩ በመግባት የውሉን ይዘት መርምሮ ቤቱ ለከሳሽ እንዲመለስ ወስኗል፡፡

በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33(1)(ረ) እንደተደነገገው የከተማው አስተዳደር የሚያስተዳድራቸው ሆኖ ለንግድ፣ ለመኖሪያ ወይም ለሌላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ካሉ የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክሶችን ተመልክቶ ለመወሰን የድሬደዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ለክሱ ምክንያት የሆነው በግለሰቦች መካከል የተደረገ ውል ሲሆን ዳኝነት ተጠይቆበት ውሳኔ የተሰጠውም ከውሉ ጋር በተያያዘ በቀረበው ክርክር ላይ ነው፡፡ ስለሆነም ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ የሚሸፈን አይሆንም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 4 ሥር እንደተመለከተውም በቀጥታ ወይም በግልፅ ካልታገዱ በቀር መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሁሉ የፍትሐ ብሔርን ክስ ተቀብለው ለማከራከር ሥልጣን አላቸው፡፡

በአጠቃላይ ጉዳዩ በፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ሊታይ ይገባል በሚል በአመልካች የቀረበው መከራከሪያ ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ እና ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ህጎች ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

www.fsc.gov.et

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 60477 ሚያዚያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12730 ሰኔ 20 ቀን 2009 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 6/2010 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

አ/ጉ